MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት
8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910
Tel: (202) 230 - 9423 ⍰ Fax:

# እ ን ተ ዋ ወ ቅ!

## 1. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የተሰኘ የሲቪክ ድርጅት መመሥረቱን ያውቃሉ? ካላወቁ እናስተዋውቅዎ፤

- ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት፣ መስከረም 26 እስከ 27 ቀን 2005 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ለሁለት ቀን በተደረገ መሥራች ጉባዔ የተመሠረተ የሲቪክ ድርጅት ነው።
- የድርጅቱ መሥራች ጉባዔ ተሳታፊዎች 93 ሲሆኑ፣ በሁለት ቀን ቆይታቸው የሞረሽ ወገኔን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ በማጽደቅ፣ ፕሮግራሙን ተግባራዊ የሚያደርጉ 31 የምክር ቤት አባላት፣ አምስት የቁጥጥርና ፍተሻ ኮሚቴ እና አሥር የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባሎችን በመምረጥ ድርጅቱ በሁለት ዓመት ሊያከናውናቸው የሚገቡ የሥራ መርሐ-ግብር በማጽደቅ ለተግባራዊነቱ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ የዐማራው ነገድ ድምፅ ነው ።
- ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ከምሥረታው ወቅት አንስቶ ባከናወነው የማደራጀትና ዓላማውን የማስፋፋት ተግባር፣ የዐማራው ነገድ ተወላጆች በሚኖሩባቸው ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ አገሮችና ከተሞች አባላትን መልምሎና አደራጅቶ መዋቅሩን በሥፋት እየዘረጋ ይገኛል። በዚህም መሠረት በአውስትራሊያ፣ በአውሮፓ፣ በዩ.ኤስ.ኤ፣ በካናዳ፣ በእስራኤል፣ በደቡብ አፍሪካ አሕጉራዊ፣ አገራዊ፣ እና ከተማ አቀፍ ኮሚቴዎች አደራጅቷል፣ አብዛኛው የነገዱ አባል በድርጅቱ ዓላማ ጥላ ሥር እስኪሰባሰብ ድረስ የማደራጀቱ ተግባር ይቀጥላል።
- የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የወጣቶችና የሴቶች ኮሚቴዎች ተመሥርተው የዐማራውን ነገድ ወጣቶችና ሴቶች በሞረሽ ወገኔ ዓላማ ሥር ለማሰባሰብ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

## 2. ሞረሽ ማለት ምን ማለት ነው?

- ሞረሽ ማለት የአደጋ ጊዜ የድረሱልኝ/ ድረሱልን መጥሪያ ቃል ነው። ቃሉ ሥራ ላይ የሚውለው፣ አንደኛ፡- አንድ የቤተሰብ አባል ወደ አንድ የታወቀ ቦታ ተልኮ መመለስ በሚገባበት ሰዓት ሳይመለስ ሲቀርና ፀሐይ ብርሃኗን ስትነሳ፣ ቤተሰቡ መመለስ በሚገባው ሰዓት ያልተመለሰውን ሰው ሁኔታ ለማወቅ፣ ይመጣበታል ተብሎ በሚገመት አቅጣጫ ከፍ ካለ ቦታ ላይ በመሆን ሞረሽ እያሉ ይጣራሉ። በስሙ ቢጠሩት፣ አንድም

ጠላት ብቻውን መሆኑን አውቆ ያጠቃዋል ከሚል ሥጋት፣ ሁለትም ስሙ ሲጠራ ስሙን ተከትሎ ርኩስ መንፈስ( ሰይጣን) ይወጋዋል ተብሎ ስለሚታመን በደፈናው ሞረሽ ተብሎ ይጠራል። ይህ እንግዲህ የጠፋን ወይም በወቅቱ ሳይመጣ የቀረን ሰው ምን አገኝቶት ይሆን በማለት ለመፈለግ የሚደረግ የሞረሽ ጥሪ ነው። ሁለተኛው የሞረሽ ጥሪ ተግባራዊ የሚሆነው፣ አንድን አካባቢ የሚያጠቃ ጠላት በድንገት ወይም በታወቀ ምክንያት ሲነሳ፣ የጥቃቱ የመጀመሪያ ሰለባ የሆነው ወገን፣ ወገኖቹ እንዲደርሱለትና እራሱንና መላውን የአካባቢው ሰው ከጥፋት ማዳን እንዲቻል የድረሱልን፣ የተጠቃን፣ የተጎዳን የመከራ ጥሪ ወይም ደወል ነው። ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅትም ይህን መጠሪያ የመረጠው ባለፉት 60 እና 70 ዓመታት በተለይ የዘረኛው የትግሬ ወያኔ አገዛዝ ዐማራውን፣ በነፍጠኝነት፣ በትምክህተኛነት፣ በገዥ እና ጨቋኝ ብሔርተኛነት ፈርጆ የኢትዮጵያ አውራ ጠላት አድርጎ መጠነ ሠፊ የሆነ፣ ግድያ፣ እስራት፣ ድብደባ፣ ከሥራ መባረር፣ መሰደድ እና ቤት ንብረት ተቀምቶ ከተለያዩ አካባቢዎች የማፈናቀል ወንጀል የተፈጸመበት በመሆኑ፤ ይህን የተቀነባበረ የዘር ማጽዳት ተግባር ፈጽሞ ለማስቀም በተናጠል የማይቻል ብቻ ሳይሆን፣ ጥፋቱ ያነጣጠረው በሁሉም የነገዱ አባላት ላይ ስለሆነ፣ ነገዱ ተባብሮ ጥቃቱን መቋቋም እንዲችል የቀረበ የድረሱልን ጥሪ ነው። ስሙ በዐማራው ነገድ ላይ የደረሰው ጥቃትና ጥቃቱን ለመቋቋም የመላውን ነገድ ትብብር የሚጠይቅ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ የዐማራው የአደጋ ጊዜ መሰባሰቢያ መጠራሪያ በመሆኑ ባህላዊና ታሪካዊ ትርጉም የያዘ ስለሆነ ተመራጭ ሆኗል።

## 3.ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ለምን ተመሠረተ?

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የተመሠረተው የሚከተሉትን እውን ለማድረግ ነው።

1) በዘረኛው የትግሬ ወያኔ አገዛዝ ቤት ንብረታቸውን ተነጥቀው ለዘመናት ከኖሩበት የደቡብ፣ የምሥራቅ፣ የምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብና የመሀል ኢትዮጵያ አካባቢዎች ለተፈናቀሉ ዐማሮች አቅም በፈቀደ መጠን ከዕለት ደራሽ እስከ ዘለቄታ ማቋቋሚያ የሚደርስ ዕርዳታ ማሰባሰብና ለተጎጂዎቹ ማድረስ፤
2) ዐማራ በመሆኑ ብቻ፣ ዘረኛው የትግሬ ወያኔ አገዛዝ በአውራ ጠላትነት ፈርጆ ዘር የማጽዳትና ዘር የማጥፋት ወንጀል እየተፈጸመበት ላለው የዐማራ ነገድ ድምፅ ለመሆን፣ የሚደርስበትንና የደረሰበትን የዘር ጥፋት፣ የኢኮኖሚ ነጠቃ፣ የመብት ገፈፋና የሰብአዊ መብቶች ረገጣ ለዓለም ኅብረተሰብ ማሰማት፤
3) ዐማራው በኢትዮጵያ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሕይዎት ውስጥ ተገቢ ቦታውን እንዲይዝ ሁለንተናዊ አቅሙን ማጎልበት፤

## 4.ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት እንዴት ተመሠረተ?

- ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የተመሠረተው፣ የትግሬ ወያኔ አገዛዝ ከየካቲት እስከ መጋቢት 2004 ዓ.ም በደቡብ ብሔር/ብሔረሰቦች ክልል በማጅ ዞን ጉራ ፈርዳ ወረዳ ይኖሩ የነበሩ ዐማሮችን፣ አገራችሁ አይደለም ብሎ በዘራቸው ብቻ፣ ከሌሎች ነገዶች ነጥሎ፣ ቁጥራቸው ከ22 ሺ በላይ የሆኑትን በአንድ ጊዜ ቤት ንብረታቸውን ነጥቆ የማባረሩ እና ከዚሁ ዞን 78 ሺ ያህል እንደሚባረሩ በዓለም የብዙኃን መገናኛ መሣሪያዎች መደመጡ፣ ቀደም ሲልም በኦሮሚያ፣ በሶማሊያ እና በአፋር ክልሎች እንደተባረሩት ሁሉ፣ የዐማራ ክልል ተብሎ ከተከለለው ጭምር በልዩ ልዩ ምክንያቶች ዐማራው የተባረረና መባረሩ የማይቀር መሆኑ በውጭ የሚኖሩ የዐማራው ነገድ ልጆች ቢዘገዩም፣ መገንዘባቸውና ይህን ለመቋቋም የዐማራው ነገድ መደራጀት አለበት ብለው ቁርጠኛ ውሣኔ ላይ መድረሳቸው ነው።

- ቁጥራቸው 13 ያህል የሆኑ በአውሮፓና በአሜሪካ የሚኖሩ ወገኖች ከፍ ሲል የተጠቀሰው አሳዛኝ፣ አስደንጋጭና አሳፋሪ ዜና እንደሰሙ፣ ከሚያዝያ 2004 ዓ.ም እስከ መስከረም 2005 ዓ.ም ድረስ

ለስድስት ወራት ያህል ግዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ መሥርተው ባደረጉት ውይይትና የህሳብ ፍጭት ዐማራውን ከፈጽሞ ጥፋት መታደግ የሚችል የዐማራው ድምፅ የሚሆን የሲቪክ ድርጅት መመሥረት እንዳለበት በመተማመን፣ የዚህን ድርጅት ፕሮግራም፣ በፕሮግራሙ መካተት ያለባቸውን ራዕዩን፣ ተልዕኮውን፣ ዓላማና ግቡን እንዲሁም የፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የአባላቱ የተግባር መመሪያ የሆነ መተዳደሪያ ደንብ በማርቀቅ የድርጅቱን ኅልውና(መመሥረት) ይፋ የሚያደርግ መሥራች ጉባዔ እንዲጠራ፣ ለጉባዔው ተሳታፊ የሚሆኑ የነገዱ አባሎችና በዓላማው የሚያምኑ እንዲመለመሉ በማድረግ፣ ከአውስትራሊያ፣ ከካናዳ፣ ከአውሮፓ እና ከዩ.ኤስ.ኤ በተመለመሉ 93 አባላት መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም ሊመሠረት ችሏል።

## 5.ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት እንዲመሠረት ያደረጉት አስገዳጅ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

ለማናቸውም ድርጅት መመሥረት መነሻ ምክንያቱ የችግሮች መፈጠርና የችግሮቹ መኖር በሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ ማግኘት ናቸው። ከዚህ አንፃር ለሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት መመሥረት መሠረታዊ ምክንያቱ ባለፉት 22 ዓመታት የትግሬ ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በዐማራው ነገድ ላይ በታቀደ፣ በተጠናና በተቀነባበረ መንገድ ያደረሰውና እያደረሰ ያለው የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ተግባር ነው። እነዚህም፡-

- ዐማራው በነፍጠኛነት፣ በትምክህተኛነት፣ በገዥ መደብና በጨቋኝ ብሔረሰብነት፣ በኢትዮጵያ ብሔርተኛነት አቀንቃኝነት(ጠበቃነት) ተፈርጆ፣ በኢትዮጵያ ተፈጠሩ ለተባሉ ችግሮች ሁሉ ተጠያቂ በማድረግ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ነገድና ጎሣዎች አውራና ደመኛ ጠላት ተደርጎ እንዲታይና ሁሉም በእርሱ ላይ የጥፋት እጁን እንዲያነሳበት በመቀስቀስና በማደራጀት ሠፊ ሥነ-ልቦናዊና አካላዊ ጥቃት እንዲደርስበት መደረጉ፤

- በኢትዮጵያ ክልሎች ተዘዋውሮ የመሥራትና የመኖር መብቱን በኃይል መነጠቁ፤

- የሌሎች ነገዶችን ቋንቋ መናገር አትችልም ተብሎ ከዐማራው ክልል ውጭ ባሉ አካባቢያዊ መንግሥታት ተብየዎች ከሥራ መባረሩ፤

- ዐማራውን ከመንግሥት ቢሮክራሲ ለማጽዳት 45 ዓመት ዕድሜ 20 ዓመት አገልግሎት የሚል የጡረታ ቀመር በማውጣት ፣ ዐማራው የዐማራ ክልል ከተሰኘው ጨምሮ ከመንግሥት መዋቅር መባረሩ፣

- የተቀነባበረ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፣ በአሶሳ፣ በደኖ፣ አሰቦት ገዳም እና በሐረርጌ ልዩ ልዩ ወረዳና ቀበሌዎች፣ አርባጉጉ፣ አረካ፣ ወተር፣ በወለጋ፣ በኢሉባቡርና በከፋ የተለያዩ ወረዳዎች ዐማራው በዘር ተነጥሎ በእሳት መቃጠላቸው፣ በጥይት በገፍ መደብደባቸው፣ መሰለባቸው፣ ነፍሰጡር እናቶች ሆዳቸው በሳንጃ ተቀዶ ሽል መሰለቡ፣ ማየት የተሳናቸው አዛውንቶች ታርደው መሰለባቸው

- ከሶማሊያ፣ ከአፋር፣ ከደቡብ ብሔር/ ብሔረሰቦች፣ ከኦሮሚያና ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልሎች ዐማራው ቤት ንብረቱን ተነጥቆ፣ የመኖርና የመሥራት ኢትዮጵያዊ መብቱን ተገፎ በግፍ መባረሩ፣

- ዐማራው በገፍ መገደሉ፣ መታሰሩ፣ መገረፉ፣ መሰደዱና በራሱ ማንነት እንዲያፍር፣ ትውልዱን አንገት ለማስደፋት ተዋራጅ ለማድረግ የተያዘው በማንነት ላይ ያነጣጠረ ዘመቻ ተከታታይ መሆን፣

- የአማራውን እምነት፣ ባህልና ቋንቋ የሚያጠፉ ድርጊቶች በየግዜው በመፈጸማቸው። ለምስሌ በቅርቡ በዋልድባ ገዳም ላይ የደረሰው ድፍረት፣ ማፍረስና በገዳሙ መነኮሳት ላይ የደረሰው ስደት፣ ግርፋትና

እስራት።

## 6. ዐማራው በዘር ተለይቶ በጠላትነት ተፈርጆ የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀል የተፈጸመበት ለመሆኑ ማሳያ ተጨባጭ መረጃዎቹ ምንድን ናቸው?

የትግሬ ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ዐማራውን በጠላትነት ፈርጆ የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸመበት መሆኑ በተጨባጭ የሚያሳዩት ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

- አንደኛ፡- የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ(ሕወሓት) ፕሮግራም፣ በዚህ ፕሮግራም የትግራይ ሕዝብ ደመኛ ጠላት "ዐማራ" እንደሆነና የትግራይ ሕዝብ ዐማራን ማጥፋት እንዳለበት በማያሻማ መንገድ የገለጸው መሆኑ፣
- ሁለተኛ፡- በመለስ ዜናዊ የተጻፈው "የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወዴት/ ግምገማ 1979" የሚለው መጽሐፍ የትግራይ አውራ ጠላት ዐማራው መሆኑንና ይህንን ብሔረሰብ ታግለው መጣል እንዳለባቸው የተገለጸው ዘረኛ አቋም ፤
- ሦስተኛ፡- ሕወሓትን ጨምሮ ሁሉም ብሔረሰባዊ ድርጅቶች የኢትዮጵያ አውራ ችግር ብሔራዊ ጭቆና ነው፣ ጨቋኙም ዐማራው ነው ብለው የሚያምኑና ይህንን ብሔር ታግለው መጣል እንዳለባቸው በየፕሮግራሞቻቸው ያሰፈሩት መሆን፣
- አራተኛ፡- በፕሮግራማቸውም መሠረት ሁሉም ብሔርተኛ ድርጅቶች ዐማራውን ከሥነ-ልቦና እስከ አካለዊ ጥቃት የደረሰ መጠነ ሠፊ ጥቃት አድርሰውበታል። በመሆኑም በ1980 በሻዕቢያና በኦነግ ጥምረት በአሶሳ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ዐማሮችን ሰብስበው ቤት ውስጥ በመዝጋት በእሳት አቃጥለው ጨርሰዋቸዋል። በአሰቦት ገዳም ይኖሩ በነበሩ ዐማሮችና ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች በሕወሓት፣ በኦነግና በኢሕዴድ ጥምረት አያሌ ዐማሮች ተጨፍጭፈዋል፣ ከነነፍሳቸው ገደል ተጥለዋል፤ በበደኖ ፣ አርባ ጉጉ፣ ወተር፣ አረካ፣ ወለጋ፣ ከፋ፣ እና አርማጭሆ ዐማሮች በዘራቸው ብቻ እየተመረጡ ተገድለዋል፣ ታስረዋል፣ አካባቢውን እንዲለቁ ተደርገዋል፣ ቤት ንብረታቸውን ተነጥቀዋል፣ ከሥራ ተባረዋል፤ ተሰደዋል፤
- አምስተኛ፡-መለስ ዜናዊ ኸርማ ኮኸን ለምን መሬትን በግል እንዲያዝ እንዳላደረጉ ላቀረበለት ጥያቄ የሰጠው መልስ፣ "መሬት ለግል ቢሰጥ ተጠቃሚ የሚሆነው ዐማራው ስለሚሆን፣ ይህ እንዳይሆን ስለማይፈለግና ዐማራውን ከመሬት ለመንቀል፣ መሬት በመንግሥት እጅ መያዝ እንዳለበት" የሰጠው መልስ፣ ኸርማን ኮኸን ከኢሣት ሳተላይት ቴሌቪዥንና ራዲዮ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ የሰጠው መልስ ነው፣
- ስድስተኛ፡-የመለስ አማካሪና የሲ.አይ.ኤ ሰው የሆነው ፖል ሄንዝ በጻፈው ዘገባ ላይ ወያኔ ፀረ-ዐማራ መሆኑንና ዐማራን ለማጥፋት የተደራጀ እንደሆነ የገለጸበት፣
- ሰባተኛ፡- የሽግግር መንግሥቱ ሲዋቀር የሁሉም ነገዶች ተወካይ ተብየዎች እንዲገኙ ሲደረግ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ እና በማዕከላዊ መንግሥት ምሥረታ ብቻ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያን ከውጭ ወራሪዎች መክቶ ያቆየ፣ በቁጥሩ ከሁሉም ነገዶች የላቀ ድርሻ ያለው የዐማራ ነገድ ያለ መወከሉ መሠረታዊ ምክንያት በጠላትነት የተፈረጀ መሆኑን ነቃሽ ነው፤
- ስምንተኛ፡- ወያኔ ዐማራን፣ አማርኛንና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማጥፋት የተደራጀና ይህንንም ሲሠራ የኖረ መሆኑን አቶ ገብረመድኅን አርኣያ የተባሉ ሰው "መጽሐፍ ቅዱስን ያቃጥሉ የነበሩ እነማን ናቸው?" በሚል ርዕስ ያቀረቡት በድኅረ ገጾች የተሰራጨ የምስክርነት ማስረጃ ሰነድና እኒህ ግለሰብ በተከታታይ ስለወያኔ ማንነትና ዓላማ ያቀረቧቸው መረጃዎች፣
- ዘጠነኛ፡- የዐማራውን እምነት፣ ባህልና ቋንቋ የሚያጠፉ ድርጊቶች በየግዜው በመፈጸማቸዉ። ለምስሌ በቅርቡ በዋልድባ ገዳም ላይ የደረሰው ድፍረት፣ ማፍረስና በገዳሙ መነኮሳት ላይ የደረሰው ስደት፣ ግርፋትና እስራት።
- አሥረኛ፡- ከደቡብ፤ ከኦሮሚያ፣ ከሶማሊያ፣ ከአፋር፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ እና ከራሱ ከዐማራ ክልል

ከወልቃይት፣ ከጠገዴ፣ ከጠለምት፣ ከሰቲት ሁመራ፣ እና ከአርማጩሆ የተባረሩ ዐማሮች፣

- አሥራ አንደኛ፡- አቶ ገሠሠው እንግዳ፣ አቶ አስገደ ገብረሥላሴ፣ አቶ ብሥራት አማረ፣ አቶ አስራት አብርሃ የተባሉ የሕወሓት አባላት የነበሩ በተከታታይ "ታሪክ አጉዳፊው የአልባኒያ ደብተራ" "ገሐዲ ቁ.1"፣ "ፍኖተ ገድል" እና "ከአገር በስተጀርባ"፣ በተሰኙ መጽሐፍቶቻቸው ወያኔ ዐማራን በጠላትነት ፈርጆ እርሱን ለማጥፋት መንቀሳቀሱንና ያጠፋውንም ሕዝብ በዝርዝር ያረጋገጡበት፣
- አሥራ ሁለተኛ፡- የወያኔ መሪዎች በተደጋጋሚ ስብሃት ነጋ፣ ሣሞራ ዩኑስ፣ ዐባይ ፀሐዬ፣ ወዘተ በተለያዩ ጊዜአቶች ዐማራና ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ላይነሳ ቀብረነዋል በማለት የሰጧቸው ቃለ ምልሶች፣
- አሥራ ሦስተኛ፡- 45 ዓመት ዕድሜ 20 ዓመት አገልግሎት በማለት ከመንግሥት ቢሮክራሲ የተባረረው ዐማራ፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከተባረሩት ነባርና በሳል አስተማሪዎች መካከል 98 በመቶ የሚሆኑት ዐማሮች መሆን፣ የመባረራቸው ምክንያት በሥራ ድክመት ሳይሆን፣ በዘር መሆኑን በተጨባጭ የሚያስይ መሆን፣
- አሥራ አራተኛ፡ በ13ኛው መደበኛ የትግራይ ነጻአውጪ ድርጅት ፓርላማ ስብሰባ ላይ ፤ የስታትስቲክስ ባለሥልጣን የሆነቸው ወይዘሮ ሳምያ ባቀረበችው የፓርላማ ዓመታዊ ሪፖርት ከ1999-2000ዓ.ም 2.4 ሚሊዮን ዐማራ ሲስተማቲክ በሆነ መንገድ ጠፍቷል ስትል ያረጋገጠቸው ምስክርነት፣ ዐማራው በጠላትነት ተፈርጆ በሰከነ መንገድ በግፍ መገደሉን የሚያረጋግጥ መረጃ መሆኑ፣
- አሥራ አምስተኛ፡- በአገር የመኖርና የመሥራት መብቱን ተገፎ በስደት ላይ ከሚገኘው ኢትዮጵያዊ የዐማራው ነገድ ቁጥር የበዛ መሆኑ፣ ይህን የወያኔው የዩናይትድ ስቴት ኦፍ አሜሪካ አምባሳደር የነበረው አቶ ካሣሁን አየለ ለአለቆቹ ባቀረበው ሪፖርት የተረጋገጠ መሆኑ፣
- አሥራ ስድስተኛ፦ ዐማራ የተባለውን ክልል ዐማሮች የማያስተዳድሩት መሆን ዐማራው በጠላትነት ተፈርጆ እንዲጠፋ መጠነ ሠፊ የሆነ የዘር ማጥፋት ወንጀል በወያኔ አገዛዝ እየተፈጸመበት እንደሆነ የሚያረጋግጡ መረጃዎች ናቸው።

## 7.የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ራዕይ ምንድነው?

- ዐማራው በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ እንደሌሎቹ ነገዶች ሁሉ፣ ኅልውናው ተጠብቆ፣ እየደረሰበት ያለው መገደል፣ መሳደድ፣ መዋረድ፣ አንገት መድፋት፣ ከቀየው መፈናቀል ቆሞ፣ በፈለገው ቦታ፣ባሻው የሥራ መስክ የመኖርና ተንቀሳቅሶ መሥራት ሁለንተናዊ መብትና ክብሩ ተጠብቆ ማየት፤
- የሕዝባዊ የዜግነት መርሆዎች/ሲቪክ ናሽናሊዝም /የተሰኙት የወል የዜግነት መገለጫ የሆኑ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና የሕግ የበላይነት ሰፍኖ ማየት፤

## 8.የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ተልዕኮ ምንድን ነው?

- የአንድ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መገለጫ የሆኑት የነባር ኢትዮጵያና ኢትዮጵዊነት መገለጫ የሆኑ ዕሴቶችና ተቋሞች ተጠብቀውና ዳብረው፣ ሁሉም የኢትዮጵያ ነገድና ጎሳዎች፣ ሃይማኖቶችና አመለካከቶች በዕኩልነት የሚታዩበት፣ መቻቻል፣ መከባበርና መደጋገፍ የሰፈነባት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ፤
- በአክራሪ የጎሳ ፖለቲከኞችና ድርጅቶች አማካኝነት በዐማራው ነገድ ላይ የተካሄደውንና በመካሄድ ላይ ያለውን የዘር ማጽዳት ዘመቻ ማስቆም፤
- ለዐማራው ነገድ ኅልውና ወሳኝ በሆኑ ዘርፎች ማለትም፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ፣

በትምህርት፣ በጤናና በመሳሰሉት መስኮች ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎችን ማቀነባበርና ዐማራው ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፤

- የኢትዮጵያ ኅልውና ምሰሶ ሆኖ የኖረው የዐማራው ነገድ፣ ለወደፊቱ የአገሪቱ ኅልውና በአስተማማኝነት መቀጠል እንዲችል፣ ተቀራራቢና ተመሳሳይ ግቦችና ዓላማዎች ካሏቸው ድርጅቶች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች ጋር በመሆን ለጋራ ብሔራዊ ዕሴቶች ዳብሮ መቀጠል ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ናቸው።

## 9. ለመሆኑ ዐማራ ማነው?

**በሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት እምነት ዐማራ ማለት የሚከተሉትን የተቀበለና ያመነ ነው።**

- ዐማራ ነኝ ብሎ የሚያምን፤
- በኢትዮጵያ በሚገኙ ማኅበረሰቦች ልዩ ልዩ ስብስቦች የተገለለ/የተገደፈ/፣
- ኢትዮጵያ ረጅም የአገራዊና የመንግሥትነት ታሪክ ያላትና በሀወርታዊ ሆና የኖረች፣ በዚህም ሀወርታዊነት መቀጠል አለባት ብሎ የሚያምን፤
- የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ምሥራታ ሂደት በዓለም ከታዩት የሚለየው በቦታ፣ በጊዜና በአድራጊ ግለሰቦች እንጂ በቀረበው በነባራዊ ሁኔታዎች አስገዳጅነት በግድ መታለፍ የነበረበት መሆኑን የሚያምን፤
- እስከዚህ ወቅት ድረስ ቋንቋን መሠረት አድርጎ እኔ ዐማራ ነኝ ብሎ ከሌሎች ተነጥሎ ያልተደራጀ፣ በሰፊዋ ኢትዮጵያ ተሰራጭቶ የሚገኝ መሆኑን ያወቀ፤
- የኢትዮጵያ አንድነትና አገራዊነት ዳብሮ መቀጠል አለበት የሚል፤
- በኢትዮጵያ አገራዊና የማዕከላዊ መንግሥት ምሥረታ የአያያዥነት/የሙጫነት/ ሚና የተጫወተ መሆኑን የተገነዘበ፤
- በተለያዩ ወቅቶች ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተነሱ ኃይሎች የጥቃት ዒላማ በመሆን ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለ፣
- በወያኔ ዘረኛ አገዛዝ፣ ነፍጠኛ፣ ትምህተኛ፣ አድኃሪ፣ ወዘተ የሚሉ የማጥላያ ስሞች ተሰጥተውት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መብትና ጥቅሞቹን የተነጠቀና የተገፈፈ ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብ ማለት ነው።

## 10. የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ዓላማና ግቦች ምንድን ናቸው?

- በዘራቸው ምክንያት ከተለያዩ የኢትዮጵያ ምሥራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብና መሀል አካባባዎች ቤት ንብረታቸውን ተነጥቀው ለተፈናቀሉ የዐማራ ነገድ አባሎች ከዕለት ደራሽ እስከ ዘለቄታ ማቋቋሚያ የሚሆን ዕርዳታ ማሰባሰብና ለተፈናቃዮች ማድረስ፣



- በዘመነ የትግሬ ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በአውራ ጠላትንት ተፈረጆ የዘር ማጽዳትና ዘር ማጥፋት ወንጀል እየተፈጸመበት ለአለው የዐማራ ነገድ ድምፅ ሆኖ ማገልገል፤
- የዐማራው ነገድ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይዎት ውስጥ ተገቢ ቦታውን እንዲይዝ ሁለንተናዊ ዐቅሙን ማጎልበት፣

## 11. የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ግብ ምንድን ነው?

- በዐማራው ላይ የተከፈተውን የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ዘመቻ ፈጽሞ ማስቆም፤
- የዐማራው ማንነት ሁለንተናዊ መገለጫ የሆኑ የወል እሴቶችን ከጥፋት መከላከል፣ በወያኔ አገዛዝ እንዲጠፉ የተደረጉትን ወደነበሩበት መመለስና ማዳበር፣
- የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት፣ ብሔራዊ ጥቅምና ለሕዝቡ ሉዐላዊነት፣ ሰላም፣ ዕኩልነትና ፍትሕን የሚያረጋግጥ የምላተ ሕዝቡን ፈቃድ ያገኘ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ከሚታገሉ ኢትዮጵያዊ ኃይሎች ጎን በመሰለፍ የበኩሉን ድርሻ ማበርከት፤
- የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በአገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም፣ የግዛት አንድነት፣ በሕዝቡ መብትና ነፃነት ላይ ያደረሰውን አገራዊ ክህደትና የፈጸመውን ወንጀል ለዓለም ኅብረተሰብ ማጋለጥ፣ አገዛዙ በሕዝባዊ አመጽ እንዲወገድ የሕዝባዊ እምቢተኝነት ስሜት በሕዝቡ ውስጥ ማስረጽ፣ ሕዝቡ የእኔ የሚለው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት መታገል፤
- በዐማራው ነገድ ላይ የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸሙ ቡድኖችንና ግለሰቦችን ለፍትሕ ማቅረብ፣

## 12. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ከሌሎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት እንዴት ይገለጻል?

የዐማራው ነገድ እየተካሄደ ባለው ዲሞክራሲያዊ ትግል አካል ሆኖ፣ ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ የበላይነት፤ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝቡ ሉዓላዊነት መረጋገጥ ከሚታገሉ ኃይሎች፣ የዐማራውን ነገድ በጠላትነት ከማይመለከቱ ወይም የፖለቲካ ሥልጣን መረማመጃ አድርገው ከማያዩት ከማናቸውም ድርጅቶች ጋር ሁሉንም ኢትዮጵያውያንን የጋራ ጥቅም በሚያስከብሩ ጉዳዮች ዙሪያ የሚጠበቅበትን ሁሉ በብቃት ለመወጣት የበኩሉን ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል።

## 13. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የሚታገለው ማነን ነው? ወይም ምንን ይቃወማል?

- ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አምርሮ የሚታገለው፣ በዘር ላይ የተመሠረተ አመለካከትን እና የትግሬ ወያኔ በዚሁ አመለካከት በመመራት ዐማራን፣ አማርኛ ቋንቋን፣ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ያደረገውንና እያደረገ ያለውን ተግባር፣ ፖሊሲና መመሪያዎችን ነው።
- ነገድና ጎሣዎችን መነሻና መድረሻ አድርጎ የተዋቀረን የፌደራል የመንግሥት አደረጃጀትን ይቃወማል፣
- በነገድ፣ በጎሣና በሃይማኖት ልዩነቶች ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ አደረጃጀትን አምሮ ይታገላል፤
- በችሎታና በዕውቀት ሳይሆን፣ በጎሣና በፖለቲካ አቋም የሚሰጡ መንግሥታዊ ኃላፊነቶችን ይቃወማል፤
- ሰዎች በዜግነታቸው ተዘዋውረው በፈለጉት ቦታና አካባቢ የመኖርና የመሥራትን መብት የሚገድብን ማናቸውንም እርምጃ ይቃወማል፣ ይታገላልም፤
- የሰዎችን የመደራጀት፣ ሀሳብን በነፃ የመግለጽ፣ የመዘዋወር፣ መብትና ነፃነቶችን የሚገፍ ወይም የሚገድብ ማናቸውንም ዓይነት ድርጊት፣ እንዲሁም ያለ ሕግ አግባብ የመያዝ፣ የመፈተሽ፣ የመበርበርን ድርጊቶችን አምርሮ ይታገላል፤
- ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነትና ፀረ-ኢትዮጵያዊነትን ይቃወማል፣ ይህንንም አቋምና አመለካከት አምርሮ ይታገላል፣

## 14. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ህልውናውን ከአገኘ ካለፉት ስድስት ወራት ጀምሮ ምን ተግባሮችን አከናወነ?

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ከተመሠረተ ከመስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ስድስትና ሰባት ወራቶች የሚከተሉትን ተግባሮች አከናውኗል።

- ድርጅቱ የሚመራባቸውን ማለትም ፕሮግራሙን፣ መተዳደሪያ ደንቡንና የደንቡን ተፈጻሚነት ማረጋገጫ የሆነ የዲስፕሊንና የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቶ በሥራ እንዲውል ተደርጓል።
- ድርጅቱ ሕጋዊ ሰውነት እዲያገኝ በተደረገው ጥረት በሜሪላንድ ስቴት ተመዝግቦ ሥራውን በሕጋዊ አግባብ እያከናወነ ይገኛል።
- የድርጅቱን መመሥረት የዐማራው ነገድ እንዲያውቅና ሁለንተናዊ ድጋፉን እንዲያደርግ በሬዲዮ፣ በፓልቶክ፣ በድኅረ-ገጾችና በሕዝባዊ ውይይቶች የማስተዋወቅ ሥራዎች ተሠርተዋል። በዚሁ ትውውቅ መሠረት በአራት አሕጉሮች (አውሮፓ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ እስያና አፍሪካ) በሚገኙ አገሮችና ከተሞች የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ኮሚቴዎች ተደራጅተው ሥራ ጀምረዋል። በዩ.ኤስ.ኤ ከሃያ በላይ ግዛቶች የሞረሽ መሠረታዊ ማኅበሮች ተደራጅተዋል።
- የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የወጣቶችና የሴቶች ኮሚቴዎች ተደራጅተዋል።
- የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክንና የሰማዕታቱ አርበኛ የአቡነ ጴጥሮስን ሀውልቶች ከመፍረስ ለመታደግ ሕዝቡ ተቃውሞን እንዲያሰማ ለማድረግ 117ኛውን የዐድዋ ድል መታሰቢያ ቀን ምክንያት በማድረግ

በዋሽንግተን ዲሲ ሕዝባዊ ስብሰባ በመጥራት ጉዳዩን የማሳወቅ ሥራ ተሠርቷል። በሕዝባዊ ስብሰባው፣ ስለ አድዋ ጦርነት ምክንያትና ውጤት፣ በአድዋ ጦርነት የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ሚና፣ የሰማዕታቱ የአቡነ ጴጥሮስና የአቡነ ሚካኤል የነፃነት ተጋድሎ ታሪክ በባለሙያተኞች ትምህርት እንዲሰጥ ተደረጓል። በራሪ ወረቀቶች ለሕዝብ ታድሏል። የሁለቱ ሀውልቶች መታሰቢያና ማነቃቂያ እንዲሆኑ አምስት ሺ በመዳሊያ መልክ ተሠረተው በመጠነኛ ዋጋ ለሽይጭ እንዲቀርቡ ተደርጓል።

- ለሕዝብና ለአባላት የሚሰራጩ ከሃያ በላይ ጥናታዊ ጽሁፎች ተዘጋጅተው እንዲሰራጩ ተደርጓል።
- በዐማራው ነገድ ላይ የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸሙ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ለዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍትሕ ይገኝ ዘንድ መረጃዎች የማሰባሰብ ሥራ በተጠናከረ መንገድ እየተሠራ ይገኛል። በዚህ አጋጣሚ ወንጀል የፈጸሙ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ማንነት የምታውቁ ያሏችሁን መረጃዎች ለሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት በመጠቆምና በማመላከት እንድትተባበሩን ወንጀል በተፈጸመበት ሕዝብ ስም አበክረን እንጠይቃለን።
- ከደቡብ፣ ከኦሮሚያ፣ ከአፋር፣ ከሶማሊያና ከቤንሻጉል ጉምዝ፣ እንዲሁም ከወልቃይት፣ ከጠገዴ፣ ከሰቲት፣እና ከጠለምት ወረዳዎች የተፈናቀሉትን ዐማሮች ማንነት፣ ብዛት፣የደረሰባቸውን በደል፣ የተነጠቁትን የንብረት መጠን ለማወቅ ባደረግነው ጥረት፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል፣ ከከማሽ ዞን ከያሶ ወረዳ በ2005 የተፈናቀሉትን ዐማሮች ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ችለናል።



በበለጠ ዝርዝር መረጃውን በድህረ- ገጻችን http://www.moreshwegenie.org ላይ ይመልከቱ።

- የትግሬ ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በዐማራው ነገድ ላይ እየፈጸመ ያለውን የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀል ዓለም አቀፍና አሕጉራዊ ድርጅቶች አውቀው በአገዛዙ ላይ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና እንዲያደርጉ የሚያስችል የተጠናከረ መረጃ በማሰባሰብ ላይ ይገኛል።

## 15. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ለወደፊቱ ምን ሊሠራ አቅዷል?

- የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የወደፊት የሥራ ዕቅድ በመሥራች ጉባዔው ለሁለት ዓመታት እንዲሠሩ ያፀደቃቸውን ተግባሮች ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር እያጣጣሙ ተግባራዊ ማድረግ ነው። ዝርዝሩን በድኅረ-ገጹ ይመልከቱ።

## 16. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ማንን ይወክላል?

ስሙ እንደሚያመለክተው ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የሚወክለው፣ በዘሩ ምክንያት በዘረኛው የትግሬ ወያኔ አገዛዝ የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀል የተፈጸመበትን የዐማራ ነገድ ነው።





## 17. ማስገንዘቢያ፡-

ዐማራው ኢትዮጵያዊነቱ ተክዶ ከመገደል፣ ከመታሰር፣ ከሥራ ከመፈናቀል ሌላ በኢትዮጵያ ምድር አትኖርም ተብሎ እንደ ክፋ አውሬ በመሳደድ ላይ ነው። ይህ ዐማራን፣ አማርኛ ቋንቋና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማጥፋት ዘመቻ የከፈተው የትግሬ ወያኔ፣ የመጨረሻ ግብ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት ስለሆነ፡-

በመጀመሪያ ዐማራው ኅልውናውን ለማስጠበቅ፣ ቀጥሎም ማተቡ፣ እምነቱና እናቱ የሆነችውን ኢትዮጵያን ከብተናና ከጥፋት ለመታደግ መደራጀት ምርጫ ሳይሆን፣ ግዴታ መሆኑን ተገንዝቦ ሞረሽ ወገኔን የዐማራ ድርጅትን እንዲቀላቀል ጥሪ እናቀርባለን።

በሁለተኛ ደረጃ፣ ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት እታገላለሁ የሚል የየትኛውም ነገድ አባል፣ ዐማራው የማይኖርባት ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ ልትሆን እንደማትችል ተረድቶ፣ ዐማራው ለኅልውናው መጠበቅ የሚያደርገውን ትግል ከመደገፍ ባሻገር፣ የትግሬ ወያኔ ፀረ-ዐማራ ብቻ ሳይሆን፣ ፀረ-ኢትዮጵያ መሆኑን በማመን፣ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የሚያደርገውን አገርና ትውልድን ከጥፋት የመታደግ እንቅስቃሴ በሙሉ ልብ ሊደግፈውና ሊያበረታታው ይገባል ።

ስለሆነም ለሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ዓላማ ስምረት ከዐማራው ነገድ አባላት፣ በኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት ከሚያምኑ ኢትዮጵያውያን የዕውቀት፣ የመረጃ፣ የሐሳብ እና የገንዘብ ድጋፋችሁ እንዳይለየን የትግሬ ወያኔ የጥቃት ሰለባ በሆነው የዐማራ ነገድ ስም አደራ እንላለን።

ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት እንታደጋለን!

ዐማራው ለእኩልነት እንጂ፣ ለተዋራጅነት አልተዘጋጀም!

አባቶቻችን አገርና ነፃነትን አስረክበውናል፤ እኛ ለልጆቻችን ምን ልናስረክባቸው አስበናል?

ወያኔ ረግጦ የሚገዛን በእርሱ ጥንካሬ ሳይሆን፣ በእኛ ድክመት ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

